

በጀርመን አገር የሚኖሩ ቁጥራቸው ከ250 በላይ የሚሆኑ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች በውጭ አገር የሚገኙ ተቃዋሚ ነን ባዮች በተለያዩ ጊዜያት የአገርን ጥቅም በሚፃረር መልኩ በሚያደርጉት ሰላማዊ ሰልፍ የኢትዮጵያን ጥሩ ገፅታ ሲያበላሹ ችላ ብሎ ማየት እንደማይገባ በቱቢንገን ከተማ መጋቢተ 12 ቀን 2001 ዓም ባደረጉት ደማቅ ሰላማዊ ሰልፍ አስታወቁ

እነዚህ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በአይነቱ የመጀመርያ የተሰኘ የድጋፍ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ከመላው ጀርመን ሲሰባሰቡ የቻሉበት ምክንያት በነዚህ ትምክህተኞች ሴራ በጀርመንዋ ቱቢንገን ከተማና በመቀሌ ከተማ መካከል ሲጀመር የነበረው የወዳጅነት ግንኙነት ወይም እህትማማች ከተሞች ሲያበላሹ በመገንዘባቸው ነው

ይህ መጋቢት12 ቀን 2001 ዓም የተካሄደው የድጋፍ ሰላማዊ ሰልፍ የተቃዋሚ ነን ባዮች ሴራ እርቃኑን ያስቀረ ሲሆን የኢትዮጵያን ጥሩ ገፅታ በማንፀባረቅ ኢትዮጵያ አሁን የምትገኝበት የልማት የዲሞክራሲና የሰላም ጎዳናዋ በእነዚህ ፅንፈኞች እንደማይኮላሽ በእነዚህ ኢትዮጵያውያን ተንፀባርቃ ል

በሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን እና ጀርመናውያን ደጋፊዎቻችን የተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ ዋና ዓላማው ተቃዋሚ ነን ባዮች በውሃ ቀጠነና ለራሳቸው ጥቅም ብቻ የሚያካሂዱት ሰላማዊ ሰልፍ ቁጭ ብሎ መመልከት «ውሸት ሲደጋገም እውነት ይመስላል» የሚለውን ሃሳብ ማኮላሸት አስፈላጊና «በቃ» መባል እንዳለባቸው ለማስገንዘብ ነው

የድጋፍ ሰላማዊ ሰልፉ ከህፃን እስከ ሽማግሌ ያካተተና በአጭር ጊዜ የታቀደ ሲሆን ይህንን የተገነዘቡ ከ20 የማይበልጡ ተቃዋሚ ነን ባዮች የኢትዮጵያን ጥቅም የሚፃረር መፈክር በመያዝ የሁለቱ ከተሞች ወዳጅነት ይበልጥ እንዲጠናከር ድጋፉን ለሚገልፅ ሰልፈኛ መቃወሚያ ያነገቡት መፈክር አገሬ ከጀርመን መንግስት መጠቀም የለባትም በማለት ያሰሙት ጩኸት ኢትዮጳያውያንና ጀርመናውያን በጣም አስገርመዋል ኢትዮጵያዊ የኢትዮጵያን ከተማ በመቃወም የወዳጅነት እድሉ ለሌላ የአፍሪቃ ከተማ እንዲሰጥ ሲጮህ በታሪክ ለመጀመርያ ሆኖ ተመዝግበዋል

የድጋፍ ሰላማዊ ሰልፉን ያስተባበሩት አምስት አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የአገርን ጥቅም ለማስከበርና ማንኛውም የኢትዮጵያን ጥቅም የሚጎዳ ለመቃ ቃ ም በቀጣይ እንዲያስተባብሩአቸው እና ኮሚቴ ሆነው እንዲቀጥሉ በሰልፈኞቹ ተወክለዋል

የጀርመናዊቱ ቱቢንገን ከተማ ከአንድ የአፍሪቃ አገር ወዳጅነት ለመፍጠር ከ30 በላይ የአፍሪቃ ከተሞች ማጣርያ ቡሃላ የኢትዮጵያዊቱ መቀሌ ለመጨረሻ ዙር ከታጩች በሁዋላ በነዚህ «ዘረኛ» ባይ ዘረኞችና ትምክህተኛ ተቃዋሚዎች ሴራ እድሉን አበላሽተውታል

አንድነት ሃይላችን ነው!

**BUNDNIS MACHT DIE SCHWACHEN STARK!**
**UNITED WE STAND AND WIN!**